ቀን
Date 12 ሐምሌ 2011

ቁጥር
Ref. No 01-38/45/82

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Trade and Industry

ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጉምሩክ ኮሚሽን
አዲስ አበባ

**ጉዳዩ፡ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በአስገዳጅነት የሚገበያዩ የግብርና ምርቶችን ይመለከታል፤**

በግብርና ምርቶች ግብይት ሥርዓት ውስጥ ትስስር ተፈጥሮላቸው በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል በአስገዳጅነት እንዲያልፉ የተደረጉ ምርቶች ከምርት ገበያው ውጭ በማንኛውም መልኩ ቢሆን ግብይት ሊፈፀምባቸው የማይችል መሆኑን በተለያዩ ጊዜያቶች ስናሳውቃችሁ መቆየታችን የሚታወስ ነው። በዋንኛነት ቡና፣ ነጭ ቦሎቄ፣ ሰሊጥ፣ ማሾና የአኩሪ አተር ምርቶች ሲሆኑ እነዚህ ምርቶች በአገሪቱ የጉሙሩክ በሮች እንዲወጡ የሚያስችላቸው የምርት ዝዉዉር የሽኝት ደብዳቤ ወይም የመላኪያ ይሁንታ አግኝተዉ ካልሆነ በስተቀር ምርቶቹ ማጓጓዝ እንደማይቻል የወጡት ግብይት ህጎች ይደነግጋሉ። ሆኖም ከአሰራር ውጪ የሚጓጓዝ ምርት ግን የግብይት ሕጎችን የሚጥሱና ስርዓቱን የሚያዛቡ በመሆናቸው ህግወጥ ንግድ ወይም ኮንትሮባንድ ንግድ ሰለሚሆን ይህንን ድርጊት ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አስተዳደራዊና ሕጋዊ እርምጃ የሚወሰድባቸው ሲሆኑ የግብይት ህጎቹ ተግባራዊ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በአጥፊዎቹ ላይ እርምጃ ሲወሰድ መቆየቱ ይታወሳል።

ሆኖም በምርቶቹ ላይ አስፈላጊዉን የምርት ዝዉዉር የሽኝት መረጃ ወይም የመላኪያ ፈቃድ አግኝተዉ ማጓጓዝ ሲገባቸዉ በተለይም በቅርብ ጊዜ የማሾ ምርት ወደ ኬኒያ ሞያሌ መስመር በኩል ባሉ የጉምሩክ መተላለፊያ ኬላዎች በሙሉ በህገወጥ ወይም በኮንትሮባንድ ንገድ እየወጣ ሀገሪቱን የወጪ ምንዛሪ ግኝት በእጅጉ እያጠፋ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ።

ስለዚህ ይህ ደብዳቤ ከደረሳቸው ቀን ጀምሮ ቡና፣ ነጭ ቦሎቄ፣ ሰሊጥ፣ እና አኩሪ አተር በተለይም ማሾ ላይ ምርት ማጓጓዝ የሽኝት ሰነድ ወይም የመላኪያ ፈቃድ በትክክል የሚያመላክት መሆኑን በማረጋገጥ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲደረግ እያሳሰብን ለአፈፃፀም እንዲረዳ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 377/2008 እና የአርንጓዴ ማሾ ምርት ግብይት አስገዳጅነትን ስለማፅናት ተጠቀሰው ደንብ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ሚንስቴር መስሪያ ቤቱ የወሰነበትን ደብዳቤ አባሪ ተደርጓል።

☎ +251-551 8025/29
+251-557 5866
✉ 704

Fax: +251-551 5411, 552 3416
+251-553 1027, 554 0286

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

ከሠላምታ ጋር

አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ ሞኝች
ሚኒስትር ዴኤታ

**<u>እንዲያውቀት (ያለአባሪ)</u> ፡-**

- ለክብርት ንግድና ኢንዱስትሪ ሚንስትር
  **<u>ንግድና ኢንዱስትሪ</u>**

**<u>ግልባጭ (ያለአባሪ)</u> ፡-**

- ለገቢዎች ሚኒስቴር
- ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
- ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ
- ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን
  **<u>አዲስ አበባ</u>**

(68)

2.7 ህዳር 2010

01.1.35/606

ለ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- አረንጓዴ ማሾ ምርት ግብይት አስገዳጅነትን ስለማጽናት

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትን አስመልክቶ በቁጥር 377/2008 ባወጣው ደንብ እና ይህንኑ ተከትሎ ሚንስቴር መስሪያ ቤታችን በወጣው የማስፍፀሚያው መመሪያ ቁጥር 010/2009 መሠረት ከነጭ ቦሎቄ በተጨማሪ ቀይ ቦሎቄና አረንጓዴ ማሾ አስገዳጅ ምርቶች ሆነው ግብይታቸው በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል ብቻ እንዲፈፀም ከሚንስቴር መስሪያ ቤታችን ጥቅምት 30 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር 01.1.35 በተጻፈ ደብዳቤ ማስታወቁ ይታወሳል፡፡

ይሁን እንጂ ከላኪዎች በቀረበው ጥያቄ መሠረት አስገዳጅነቱ ለተወሰነ ወቅት እንዲነሳ መደረጉ አይዘነጋም፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የአረንጓዴ ማሾ ምርት የሚሰበሰብበት ጊዜ በመሆኑ እና አገራችንም ከዚህ ምርት የሚፈለገዉን የውጭ ምንዛሬ ማግኘት እንድትችል ወደ ምርት ገበያ በአስገዳጅነት መግባቱ ታምኖበታል፡፡

በመሆኑም የምርት ግብይቱ በምርት ገበያ በኩል ብቻ እንዲፈፀም ይህ መመሪያ የተላለፈ መሆኑን ተገንዝባችሁ አስፈላጊዉን ዝግጅት በማድረግ ተግባራዊ እንድታደርጉ እያስታወቅን፤ የዚህ ደብዳቤ ግልባጭ የደረሳችሁ የፌደራል እና የክልል የመንግስት አካላትም ወደ ውጭ የሚላከዉ አረንጓዴ ማሾ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የግብይት መድረክ ስለመገዛቱ አስፈላጊዉ ክትትል እንዲደረግ እንዲሁም የክልል የመንግስት ተቋማትም የዚህን ምርት እንቅስቃሴ በጥብቅ ቁጥጥር እንዲያደረግ እና ግብይቱም በግልጽ የግብይት መድረክ እንዲፈጸም አስፈላጊዉ ጥንቃቄና ክትትል እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

አለሚቱ ምትኩ ከርኃ ምኝኝ
ሚኒስትር ዴኤታ

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

67

<u>እንዲያውቁት፡-</u>

- ለክብርት ሚኒስትር
- ለክቡር የንግድ አሰራርና ሬጉላቶሪ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ
- ለክቡር የኢንድስትሪ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ
- ለሰብል ምርቶች ግብይት ዳይሬክቶሬት

<u>ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር</u>

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለገቢዎች ሚኒስቴር
- ለብሔራዊ ባንክ
- ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ግብይት ፈፃሚዎች ማህበር
- ለጥራጥሬ፣ቅባት እህሎችና ቅመማቅመም አዘጋጅቶ ላኪዎች ማህበር
- ለጉሙሩክ ኮሚሽን

<u>አዲስ አበባ</u>

- ለአማራ ብ/ክ/ መንግስት የንግድ ኢንዱስትሪና ግብይት ልማት ቢሮ

<u>ባህር ዳር</u>

- ለትግራይ ብ/ክ/ መንግስት የንግድ ኢንዱስትሪና ግብይት ልማት ቢሮ

<u>መቀሌ</u>

- ለኦሮሚያ ብ/ክ/ መንግስት ንግድ ኢንዱስትሪና ግብይት ልማት ቢሮ

<u>ፊንፊኔ</u>

- ለደ/ብ/ብ/ህ/ብ/ክ መንግስት ንግድ ኢንዱስትሪና ግብይት ልማት ቢሮ

<u>ሀዋሳ</u>

- ጋምቤላ ብ/ክ መንግስት ንግድ ኢንዱስትሪና ግብይት ልማት ቢሮ

<u>ጋምቤላ</u>

- ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/ መንግስት ንግድ ኢዱስትሪና ግብይት ልማት ቢሮ

<u>አሶሳ</u>

<u>እንዲያውቁት፡-</u>

- ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Trade

ቀን 10 ታህሳስ 2009
Date

ቁጥር 01135/8062
Ref. No.

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ለኢ.ፌ.ድ.ሪ ፖሊስ ኮሚሽን

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ <u>የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ዝዉዉርና ቁጥጥር አፈፃፀምን ይመለከታል ፡፡</u>

በህግ ማዕቀፍ የሚመራ ዘመናዊ የግብይት ስርዓት በመዘርጋት በህገ ወጥ/በኮንትሮባን ንግድ የሚባክነዉን የጥራጥሬ ምርቶች በመከላከልና በመቆጣጠር ፍትሃዊ የግብይት ስርዓት እንዲፈጠር በማድረግ ለአለም ገበያ የጥራጥሬ ምርቶችን በጥራትና በመጠን በማቅረብ የዉጪ ምንዛሪ ግኝታችንን ለማሳደግ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ደንብ ቁጥር 377/2008 እና መመሪያ ተዘጋጅቶ ፀድቋል፡፡

በመሆኑም የግብይት ስርዓት ከተዘረጋለት የነጭ ቦሎቄ ምርት በተጨማሪ የቀይ ቦሎቄ እና የማሾ ምርቶች ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት ከተገዙ በኂላ ወደ ኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት ብቻ ቀርበዉ ግብይት የሚፈፀምባቸዉ መሆኑ ታዉቆ ከተፈቀደዉ የግብይት ቦታ ዉጪ ሲጓጓዙ ወይም ግብይት ሲፈፀም ከተገኘ እንደ ህገወጥ ንግድ ተወስዶ አስፈላጊዉ ቁጥጥር እንዲደረግ እንዲሁም ሌሎች የጥራጥሬ ምርቶች እንደ ምስር፣አተር ፣ ሽምብራ ፣ ባቄላ ፣ አኩሪ አተር ፣ ዥንጉርጉር ቦሎቄ ፣ ፒንቶቢን ፣ ቡላ ጠፍጣፋ ቦሎቄ ፣ ጓያ ፣ ግብጦ እና የእርግብ አተር ምርቶች ምርቱ በሀገር ዉስጥ ከሚመረትበት ወደ ተጠቃሚ አካባቢ ለግብይት ሲዘዋወር ህጋዊ የዝዉዉር ወይም የማጓጓዣ መሸኛ ሰነድ እና ንግድ ፍቃድ ያሚሉ ጅምላ ነጋዴ ፣ ሸማች ተቋማት ወይም ድርጅት ወይም ማህበራት ብቻ ምርቱን ወደ ተፈቀደላቸዉ አካባቢ የማጓጓዝና ለግብይት ማቅብ የሚችሉ መሆኑ ታዉቆ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ በተላከዉ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ደንብና መመሪያ መሰረት ክትትል እና ቁጥጥር እንዲደረግ እናሳስባለን ፡፡

ከሰላምታ ጋር

<u>እንዲያዉቁት</u>

በገቢ.ና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
በገቢ.ና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለጅጅጋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
በገቢ.ና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለሁመራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
በገቢ.ና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለድሬደዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
በገቢ.ና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለባህርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
በገቢ.ና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
በገቢ.ና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለመቋሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
በገቢ.ና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለደሴ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

☎ +251-11-551 80 25-29
✉ 704

Fax +251-11-551 54 11
+251-11-551 50 27
+251-11-552 2419

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
**Ministry of Trade**

ቀን 10 ታህሳስ 200[illegible]
Date

ቁጥር 01-1-35/8062
Ref. No.

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ለኢ.ፌ.ድ.ሪ ፖሊስ ኮሚሽን

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ <u>የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ዝዉዉርና ቁጥጥር አፈፃፀምን ይመለከታል ፡፡</u>

በህግ ማዕቀፍ የሚመራ ዘመናዊ የግብይት ስርዓት በመዘርጋት በህገ ወጥ/በኮንትሮባን ንግድ የሚባክነዉን የጥራጥሬ ምርቶች በመከላከልና በመቆጣጠር ፍትሃዊ የግብይት ስርዓት እንዲፈጠር በማድረግ ለአለም ገበያ የጥራጥሬ ምርቶችን በጥራትና በመጠን በማቅረብ የዉጪ ምንዛሪ ግኝታችንን ለማሳደግ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ደንብ ቁጥር 377/2008 እና መመሪያ ተዘጋጅቶ ፀድቋል፡፡

በመሆኑም የግብይት ስርዓት ከተዘረጋለት የነጭ ቦሎቄ ምርት በተጨማሪ የቀይ ቦሎቄ እና የማሾ ምርቶች ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት ከተገዙ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት ብቻ ቀርበዉ ግብይት የሚፈፀምባቸዉ መሆኑ ታዉቆ ከተፈቀደዉ የግብይት ቦታ ዉጪ ሲጓጓዙ ወይም ግብይት ሲፈፀም ከተገኘ እንደ ህገወጥ ንግድ ተወስዶ አስፈላጊዉ ቁጥጥር እንዲደረግ እንዲሁም ሌሎች የጥራጥሬ ምርቶች እንደ ምስር፣አተር ፣ ሽምብራ ፣ ባቄላ ፣ አኩሪ አተር ፣ ዥንጉርጉር ቦሎቄ ፣ ፒንቶቢን ፣ ቡላ ጠፍጣፋ ቦሎቄ ፣ ጓያ ፣ ግብጦ እና የእርግብ አተር ምርቶች ምርቱ በሀገር ዉስጥ ከሚመረትበት ወደ ተጠቃሚ አካባቢ ለግብይት ሲዘዋወር ህጋዊ የዝዉዉር ወይም የማጓጓዣ መሸኛ ሰነድ እና ንግድ ፍቃድ ያሟሉ ጅምላ ነጋዴ ፣ ሸማች ተቋማት ወይም ድርጅት ወይም ማህበራት ብቻ ምርቱን ወደ ተፈቀደላቸዉ አካባቢ የማጓጓዝና ለግብይት ማቅብ የሚችሉ መሆኑ ታዉቆ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ በተላከዉ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ደንብና መመሪያ መሰረት ክትትል እና ቁጥጥር እንዲደረግ እናሳስባለን ፡፡

ከሰላምታ ጋር

እያና ዘውዴ
ሚኒስትር ዴኤታ

<u>እንዲያዉቁት</u>

በገቢና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
በገቢና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለጅጅጋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
በገቢና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለሁመራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
በገቢና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለድሬደዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
በገቢና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለባህርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
በገቢና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
በገቢና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለመቋሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
በገቢና ወጪእቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለደሴ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

Ministry Of Trade & Industry Archives

☎ +251-11-551 80 25-29
✉ 704
Fax +251-11-551 5411
+251-11-553 1027
+251-11-552 2419
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፵፰
አዲስ አበባ የካቲት ፳፭ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.48
ADDIS ABABA 4th March, 2016

ደንብ ቁጥር ፫፻፸፯/፳፻፰ ዓ.ም

"የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ......ገጽ ፰ሺ፱፻፲፩

Regulation No.377/2016

Pulses Transaction Council of Ministers Regulation......Page 8911

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፸፯/፳፻፰

## ስለጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፳፻፯ አንቀጽ ፭ እና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፶/፲፱፻፺፱ (በአዋጅ ቁጥር ፮፻፷፭/፳፻፪ እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፴፩(፪) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፸፯/፳፻፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጉም

በዚህ ደንብ ውስጥ ፦

፩/ "የጥራጥሬ ምርቶች" ማለት ከነጭ ቦሎቄ ውጭ ያሉ የተለያዩ የቦሎቄ ዝርያዎች፣ ማሾ፣ አኩሪ አተር፣ ምስር፣ ባቄላ፣ ሽምብራ፣ አተር፣ ጓያ፣ ግብጦ እና የመሳሰሉት ናቸው፤

፪/ "የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከል" ማለት ለጥራጥሬ ምርቶች መገበያያነት እንዲሆን አግባብነት ባለው የክልል አካል የተከለለ ስፍራ ነው፤

Council of Ministers Regulation No. 377/2016

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR PULSES TRANSACTION

This Regulation are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 and Article 31(2) of the Ethiopian Commodity Exchange Proclamation No.550/2007 (as amended by Proclamation No. 665/2010).

### PART ONE
### GENERAL

1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Pulses Transaction Council of Ministers Regulation No.377 /2016".

2. Definition

In this Regulation:

1/ "pulses" means pea beans varieties other than white pea beans, mung beans, soya beans, lentils, fava beans, chick peas, field peas, grass peas, lupine beans and the like;

2/ "primary transaction centers" means places designated by an appropriate regional organ for pulses transaction;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 35.20

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

፲፫/ "አሳሳች ድርጊት" ማለት የጥራጥሬ ምርቶች ዋጋን፣ መጠንን፣ ጥራትን ወይም ዓይነትና ዝርያን እንዲሁም የነዚህን ማንኛውንም መረጃ በተመለከተ የግብይት ተዋንያንና የሚመለከታቸው አካላትን ሊያሳስት ወይም ሊያታልል የሚችል ወይም የሃገሪቱን የጥራጥሬ ምርቶች ተቀባይነት የሚቀንስ ተግባር ነው፤

፲፬/ "ማዘጋጀት" ማለት የጥራጥሬ ምርቶችን አበጥሮና ከባዕድ ነገር አፅድቶ ለገበያ ለማቅረብ ማሰናዳት ነው፤

፲፭/ "አግባብነት ያለው የክልል አካል"ማለት ንግድን ለመምራት ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው።

፲፮/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፯/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የንግድ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፰/ "አግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት" ማለት የጥራጥሬ ምርቶችን ለማዘጋጀት፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ ወይም ለማቀናበር ወይም ለመሰል ተግባራት የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፤

፲፱/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በጥራጥሬ ሰብሎች አምራቾች እና የግብይት ተዋንያን ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት
## የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት

፬. የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት

፩/ በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የአቅርቦት ጥራጥሬ ምርት ግብይት ሻጭ በሆን አምራች እና ገዢ በሆን ሸማች ወይም ጅምላ ነጋዴ ወይም አቀናባሪ ወይም ቸርቻሪ ነጋዴ ወይም አቅራቢ መካከል ብቻ የሚከናወን ይሆናል።

፪/ አግባብነት ያለው የክልል አካል በጥራጥሬ ምርት ግብይት ጉዳይ በሕግ ሥልጣን ከተሠጣቸው ከሌሎች አካላት ጋር በመመካከር በጥራጥሬ ምርቶች አምራች አካባቢ የሚከለሉትን የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ብዛትና ሥርጭት ይወስናል።

13/ "manipulation" means any act that result or is likely to result in confusion or deception of market actors or the concerned body in relation to the price, quantity, quality or type of pulses and any information related to same and any act diminishing acceptability of the country's pulses;

14/ "preparation" means making ready pulses for market after winnowing and making it clean from any foreign materials;

15/ "appropriate regional organ" means the regional organ vested with the power to lead trade activities;

16/ "region" means any regional state referred to in Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

17/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Trade, respectively;

18/ "appropriate sector office" an organ that is empowered to issue certificate of competence to prepare, store, transport, or process or to carry out other related activities in relation to pulses transaction;

19/ "person" means a natural or juridical person;

20/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. Scope of Application

This Regulation shall apply to producers and transaction actors of pulses.

## PART TWO
## PULSES TRANSACTIONS

4. Primary Transaction Centers

1/ Pulses transaction at primary transaction centers shall be effected only between pulses producers as a seller and consumer or wholesaler or processer or retailer or supplier of pulses as a buyer.

2/ The appropriate regional organ shall, in consultation with other relevant organs mandated for transaction pulses, determine the number and distribution of primary transaction centers in pulses producing areas.

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

## ክፍል ሦስት

## ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና ስለግብይት ተዋንያን ግዴታዎች

### ፮. ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መያዝ ያለባቸውን ግብይት ተዋንያን ዝርዝር እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ አግባብ ያለው ሴክተር መስሪያ ቤት በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

### ፯. በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የተሠማራ ሰው ግዴታዎች

ማንኛውም በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ሥራ ላይ የተሠማራ ሰው ፦

፩/ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ እና ፭ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ወይም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ የማካሄድ፤

፪/ አግባብ ያለው አካል ለሥራው አፈጻጸም የሚያወጣቸውን መመሪያዎች የማክበርና የመፈፀም፤

፫/ ለግብይት ካዘጋጃቸው የጥራጥሬ ምርቶች ለጥራት ምርመራ አገልግሎት ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና በነፃ የማቅረብ፤

፬/ የየዕለቱን የጥራጥሬ ምርቶች ግዥና ሽያጭ መጠን፤ ደረጃና የዋጋ ዝርዝር እና ለግብይት ሥርዓቱ ጠቃሚ የሆኑ ማንኛቸውንም መረጃዎች መዝግቦ የመያዝና በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሲጠየቅ የማሳየት፣ እንዲሁም ድርጅቱን በአካል በመገኘት ለመጎብኘት ወይም ክምችቱን ለማወቅ ሲፈለግ የመተባበር፤

፭/ አሳሳች የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት እና ሕገወጥ ዝውውር ከመፈፀም የመቆጠብ።

### ፰. የአቅራቢ ግዴታዎች

ማንኛውም አቅራቢ ፦

፩/ ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የገዛውን የጥራጥሬ ምርት በምርት ዘመኑ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለማቅረብ የመሸጥ፤

፪/ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚያቀርበው የአቅርቦት የጥራጥሬ ምርት ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን የማረጋገጥ፤

፫/ የአንድን አካባቢ የጥራጥሬ ምርቶች ከሌላ አካባቢ የጥራጥሬ ምርቶች ጋር ሳያደባልቅ የመሸጥ፤

## PART THREE

## CERTIFICATE OF COMPETENCE AND OBLIGATION OF PULSES TRANSACTION ACTORS

### 6. Certificate of Competence

The lists of transaction actors' subject to obtain certificate of competence and issuance of certificate of competence shall be determined by directive to be issued by appropriate sector office.

### 7. Obligations of Person Involved in Pulses Transaction

Any person involved in pulses transaction shall:

1/ effect pulses transaction only at primary transaction centers and the Ethiopia Commodity Exchange in accordance with Article 4 and 5 of this Regulation;

2/ comply with all directives issued by the appropriate body for the proper execution of transaction;

3/ submit without any payment a representative sample from pulses prepared for transaction when so requested for quality inspection purposes;

4/ maintain a register of details of the daily pulses transaction quantity, grade and price and disclose the same to the relevant Government organ on demand and cooperate when physical presence for site visit or inventorying is required; and

5/ abstain from deceptive transaction and illegal transportation of pulses.

### 8. Obligations of Suppliers

Any supplier shall have the following obligations:

1/ sell the pulses purchased from primary transaction centers at the Ethiopia Commodity Exchange within the same harvest year;

2/ ensure that the pulse submitted to the Ethiopia Commodity Exchange conforms to quality standard;

3/ supply for sell pulses from a particular origin without mixing it with pulses of other origins;

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

፬/ ለጥራጥሬ ምርቶች ማከማቻነት በተፈቀደ መጋዘን ብቻ የጥራጥሬ ምርቶች የማከማቸት፣

፭/ የጥራጥሬ ምርቶችን የጥራት ደረጃውን በጠበቀ ከረጢት የማከማቸት እና ጥራቱን በማይቀንስ ወይም በማያበላሽ ሁኔታ የማጓጓዝ፣

ግዴታዎች አሉበት።

## ፲፩. የአገልግሎት ሰጪ ግዴታዎች

ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ ፦

፩/ አግባብ ያለው ሴክተር መስሪያ ቤት ለአገልግሎቱ አሰጣጥ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች የማክበርና የመፈፀም፣

፪/ የተከለከሉ ተግባራትንና አሳሳች የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት እና ዝውውርን ከመፈፀም የመቆጠብ፣

፫/ ከሚያዘጋጀውና ከሚያጓጉዘው የጥራጥሬ ምርት ለጥራት ምርመራ አገልግሎት ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና በነፃ የማቅረብ፣

፬/ ወደ ውጭ አገር የሚላኩ የጥራጥሬ ምርቶችን በአገሪቱ የጥራት ደረጃ መሠረት ወይም በአገሪቱ የጥራት ደረጃ ያልወጣላቸው ከሆነ በገዥው ጥራት ደረጃ መሠረት የማዘጋጀት፣

፭/ የጥራጥሬ ምርቶችን ምርት ከአምራች አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ወደ ወደብ ሲያጓጉዝ በሚመለከተው አስፈጻሚ አካል በፕሎምፕ የማሳሸግና የተሰጠውን መሸኛ የመያዝ፣

፮/ የጥራጥሬ ምርቶችን ከማስጫኑ በፊት አሽከርካሪው እና ተሽከርካሪውን በዚህ ደንብና ደንቡን ተከትለው በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት መሠማራታቸውን የማረጋገጥ፣

፯/ የጥራጥሬ ምርቶች ማዘጋጃና ማከማቻ ድርጅቱ እና የመገልገያ መሣሪያዎቹ ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን በሚመለከታቸው አካላት የተሰጠ ማረጋገጫ የመያዝ፣

ግዴታዎች አሉበት።

## ፲፪. የአምራች ግዴታዎች

፩/ ማንኛውም አምራች ከራሱ ማሳ ያመረተውን የጥራጥሬ ምርት በመጀመሪያ ደረጃ የጥራጥሬ ምርት ግብይት ማዕከላት ወይም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ የመሸጥ ግዴታ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም አምራች ከራሱ ማሳ ያመረተውን የጥራጥሬ ምርት በግሉ ወይም አባል በሆነበት የህብረት ሥራ ማኅበር በኩል በቀጥታ ወደ ውጭ መላክ ወይም በማቀነባበር ለገበያ ማቅረብ ይችላል።



4/ store pulses only in the warehouse authorized for pulses storage, and

5/ store pulses in a standard quality bag and transport it in a manner that may not compromise or diminish quality of pulses.

## 11. Obligation of Service Providers

Any service provider shall have the following obligations:

1/ comply with all directives to be issued by the appropriate sector office for the proper provision of service;

2/ abstain from any prohibited acts and deceptive transactions and transportation of pulses;

3/ submit without any payment a representative sample from the pulses he prepare or transport when so requested for quality inspection purpose;

4/ process export pulses in accordance with the country's quality standard or; quality standard of the buyer, if there is no quality standard of the country;

5/ have sealed by the appropriate executive body and obtain a letter of release from such body, when transporting pulses from the production area to the Ethiopia Commodity Exchange or to the port;

6/ ensure before loading pulses for transportation that a vehicle and its driver comply with the provision of this Regulation and directives issued pursuant to this Regulation;

7/ keep approval document issued by appropriate body that his pulses processing and storage facility as well as equipment maintain the required standard..

## 12. Obligation of Producer

1/ Any producer shall have the obligation to sale pulses produced from his own farm at a primary transaction centers or the Ethiopia Commodity Exchange.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, any producer may, by himself or through a cooperative society in which he is a member, directly export or process and supply for market pulses produced from his own farm.

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

፭/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ መሠረት መወሰድ በባለሀብቱው ተከታታይ እርምጃዎች ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው የክልሉ አካል የሚሰጠውን ትዕዛዝ በመከታተል ይፈፅማል።

## ፲፮. ሕገ ወጥ ድርጊቶችን ስለመጠቆም

፩/ ማንኛውም ሰው በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት፣ አዘገጃጀት፣ ክምችት ወይም ማጓጓዝ ሂደት ላይ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም ደንቡን ለማስፈፀም የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ሕገ ወጥ ድርጊት መፈፀሙን ሲያውቅ በአካባቢው ለሚገኝ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ ወይም ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል መጠቆም ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጥቆማ አቅርቦ ሕገ ወጥ ድርጊት የተፈፀመበትን የጥራጥሬ ምርት ያስያዘ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ (፬)(ለ) መሠረት የጠቋሚ አበል ይከፈለዋል።

## ፲፯. ስለተያዙ የጥራጥሬ ምርቶች እና ስለታሸጉ ማከማቻ መጋዘኖች

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፭(፫) መሠረት የጥራጥሬ ምርት የተያዘበት ወይም የጥራጥሬ ምርቶች ማከማቻ መጋዘኑ የታሸገበት ማንኛውም ሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል።

፪/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልሉ አካል ተቃውሞውን ከአንድ ሣምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መርምሮ ውሳኔ በጽሁፍ ይሰጣል። የሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል ውሳኔ ፦

ሀ) የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚሽር ከሆነ ወዲያውኑ የተያዘው የጥራጥሬ ምርቱ ለአመልካቹ እንዲመለስ ወይም የተከማቸ በት መጋዘን እሽግ እንዲነሳ ይደረጋል፤ ወይም

ለ) የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚያፀና ከሆነ የጥራጥሬ ምርቱን ናሙና በማስቀረት የአቅርቦት የጥራጥሬ ምርት ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ለአቅራቢዎች ወይም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለላኪዎች ወይም ለኤክስፖርት የተዘጋጀ የጥራጥሬ ምርት ከሆነ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለላኪዎች እንዲሸጥ ተደርጎ ገንዘቡ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው የክልል

5/ follow up and implement instructions of the Ministry or the appropriate regional organ for taking subsequent actions in according with Article 17 of this Regulation.

## 16. Whistle Blowing

1/ Any person who is aware of an illegal act committed, in violation of the provisions of this Regulation or directives issued for the implementation of this Regulation, in the course of transaction, processing, storing or transporting pulses may inform the same to the nearest pulses quality and transaction inspector or to the Ministry or the appropriate regional organ.

2/ Any person who has submitted information in accordance with sub-article (1) of this Article that led to the seizure of pulses subject to the illegal act shall be entitled to the payment of whistle blower's commission pursuant to Article 17(4)(b) of this Regulation.

## 17. Seized Pulses and Sealed Warehouses

1/ Any person whose pulses has been seized or his pulses warehouse had been sealed under Article 15(3) of this Regulation may submit his objection, in writing, to the Ministry or appropriate regional organ within five working days.

2/ The Ministry or the appropriate regional organ shall, within not exceeding one week, examine and give decision in writing on the objection. Where the decision of the Ministry or the appropriate regional organ:

a) disapproves the actions of the inspector, the release of the seized pulses or the opening of the sealed pulses warehouse shall be immediately effected;

b) approves the actions of the inspector, the pulses shall, after retaining sample, be sold to suppliers at primary transaction centers or to exporters at the Ethiopia Commodity Exchange where it is supply pulses, or to exporters at the Ethiopia Commodity Exchange where it is export pulses, and the proceeds of

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር Ministry Of Trade & Industry Archives መዝገብ ቤት

፬/ የጥራጥሬ ምርቶችን በማንኛውም አቅራቢ ወይም ጅምላ ነጋዴ ወይም ላኪ ከአንድ የምርት ዘመን በላይ ወይም በማንኛውም ላኪ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ (፫) ከተመለከተው የጊዜ ገደብ በላይ ማከማቸት፤

፭/ በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው የጥራጥሬ ምርቶችን እንዲያከማች ከተፈቀደለት መጋዘን ውጭ ማከማቸት፤

፮/ በጥራጥሬ ምርቶች የማጓጓዝ ሥራ ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው የጥራጥሬ ምርቶችን ንፅህና በጎደለው ሁኔታ ወይም ሕጋዊ የማጓጓዣ ፈቃድ በሌለው ተሽከርካሪ ማጓጓዝ፤

፯/ በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ላይ የተሰማራ ወይም ከጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ባለው ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ያለአግባብ ጥቅም ለማግኘት ሆን ብሎ አሳሳች ድርጊት መፈፀም፤

፰/ ይህንን ደንብ እና ደንቡን ተከትሎ የሚወጡ መመሪያዎችን ያለማክበር፤

፱/ የሀገሪቱን የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚያጎድፍ ማንኛውንም ድርጊት መፈፀም፤

፲/ በገባው ውል መሠረት የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ያለመፈፀም፤

፲፩/ በተቆጣጣሪ ወይም ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት የሚጠየቀውን መረጃ ያለመስጠት ወይም የተጭበረበረና የተዛባ መረጃ መስጠት።

## ፲፱. አስተዳደራዊ ቅጣት

በዚህ የቅጣት ድንጋጌ ውስጥ ያልተካተቱ ጥፋቶች አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የሚያስቀጡ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ፦

፩/ የጥራጥሬ ምርቶች ግዥ ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ውጭ የፈፀመ ማንኛውም አቅራቢ፣ ጅምላ ነጋዴ፣ ቸርቻሪ ነጋዴ፣ ላኪ ወይም አቀናባሪ የጥራጥሬ ምርቱን ከመውረስ በተጨማሪ ብር ፲ ሺህ መቀጮ ይቀጣል፤

፪/ የጥራጥሬ ምርቶችን ከተፈቀደላቸው የማከማቻ ቦታ ውጭ ያከማቸ ወይም ከተፈቀደ የማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ውጭ ሲያዘጋጅ የተገኘ ማንኛውም ሰው የጥራጥሬ ምርቱን ከመውረስ በተጨማሪ ብር ፯ ሺህ መቀጮ ይቀጣል፤

4/ storing, by any supplier or wholesaler or exporter, pulses for more than one harvest year, or by any exporter for a period exceeding the time limit specified under Article 9 (3) of this Regulation;

5/ storing, by any person engaged in the pulses trading business, pulses outside the authorized warehouse;

6/ transporting, by any person engaged in the pulses transporting business, pulses in a manner that is below the standard of cleanliness or by a person that has no valid transportation permit;

7/ any person engaged in the pulses trading business or person directly or indirectly connected to the pulses trading business, engaging in any deliberate deception for inappropriate benefit;

8/ violating this Regulation and directives issued here under;

9/ engaging in any activity detrimental to trading of pulses;

10/ failing to perform a contract of pulses trading as agreed;

11/ failing to provide information requested by inspector or appropriate organ or providing fraudulent and misleading information.

## 19. Administrative Penalty

Without prejudice to penalties provided for in other relevant law for violations not included in this penalty provisions:

1/ any supplier, wholesaler, retailer, exporter or processor who conducts pulses transaction outside the primary transaction centers or the Ethiopia Commodity Exchange shall, in addition to confiscation of his pulses, be punishable with a fine of Birr 10,000;

2/ any person, who stores pulses outside the authorized storage place or process outside the authorized processing industry shall, in addition to confiscation of the pulses, be punishable with a fine of Birr 7,000;

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር Ministry Of Trade & Industry Archives መዝገብ ቤት

የምስክር ወረቀት እስኪያገኝ ድረስ ባለው የፀና የንግድ ፈቃድ ሥራውን ማካሄድ ይችላል፡፡

**፳፫. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦችና መመሪያዎች**

የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ ወይም የተለምዶ አሰራር በዚህ ደንብ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

፩/ ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም እያንዳንዱ የጥራጥሬ ምርት ግብይት በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግብይት መካሄድ የሚጀምርበት ቀን በሚኒስቴሩ ይወሰናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፳፭ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

appropriate regional organ within two months from the effective date of this Regulation.

**23. Inapplicable Regulations and Directives**

Without prejudice to the Sesame or White Pea Beans Council of Ministers Regulation, no regulation or directive or customary practice shall, in so far as they are inconsistent with this Regulation, be applicable with respect to matters provided for by this Regulation.

**24. Effective Date**

1/ This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazetee.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the date on which the pulses transaction begin to be conducted in Ethiopia Commodity Exchange in accordance with the provision of this Regulation shall be determined by the Ministry.

Done at Addis Ababa, this 4th Day of March, 2016

HAILEMARIAM DESALEGN
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

183

# የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት መመሪያ ቁጥር 010/2009

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 377/2008 ለማስፈጸም ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

1 አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ"የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ደንብን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2 ትርጓሜ

በቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉት ቃላት ስለ ጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የወጣውን ደንብ ቁጥር 377/2008 የተሰጠዉ የቃላት ትርጉም ለዚህ መመሪያ ያገለግላል፡፡

## ክፍል ሁለት

### ስለ ጥራጥሬ ምርቶች አገልግሎት አሰጣጥ

3 የጥራጥሬ ምርቶች አዘገጃጀት

3.1 የአቅርቦት የጥራጥሬ ምርቶች አዘገጃጀት

3.1.1 የጥራጥሬ ምርቶች የጥራት ደረጃውን ፣ የተፈጥሮ ቀለሙን በጠበቀ እና የዘር መጠን በተስተካከለ ሁኔታ መዘጋጀት አለበት ፣

3.1.2 የጥራጥሬ ምርቶች በሚዘጋጁበት ወቅት የእርጥበት መጠናቸዉ ከ13 በመቶ መብለጥ የለበትም፣

3.1.3 የጥራጥሬ ምርቶች በሚዘጋጅበት ጊዜ ከምርቱ ባህሪ ጋር የማይስማሙ እና የምርቱን ይዘት ከሚቀይሩ ከማንኛዉም ባዕድ ነገሮች የፀዱ መሆን አለባቸዉ፣

3.1.4 የጥራጥሬ ምርቶች በሚዘጋጅበት ጊዜ በጥራት ደረጃቸዉ እና በባህሪያቸዉ የተለያዩ፣ የአንዱን አካባቢ ምርት ከሌላ አካባቢ ምርት፣ የአንዱን ምርት ዘመን ከሌላዉ ምርት ዘመን እንዲሁም በበልግ የተመረተ በመኸር ከተመረተ ምርት ጋር ሳያቀላቅል መዘጋጀት አለባቸዉ፣

3.1.5 የጥራጥሬ ምርቶች ዝግጅት ሲጠናቀቅ ይህን ለመቆጣጠር በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል የተዘጋጀዉ መጠንን፣ የተለዩ ገለባና እና ባዕድ ነገሮችን ለይቶ ማስቀመጥ አለበት፣

ንግድ ሚኒስቴር Minisstry of Trade Archives መዝገብ ቤት
ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives መዝገብ ቤት
ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር Ministry Of Trade & Industry Archives መዝገብ ቤት

እንዲሁም ቆዳና ሌጦ ከመሳሰሉት ባዕድ ነገሮች ነፃ በሆነ ሁኔታ መዘጋጀት አለበት፣

3.3.3 ተመሳሳይ የባህሬ አይነትና ዝርያ ካለቸዉ የጥራጥሬ ምርቶች ዉጨ ቀላቅሎ ያለማዘጋጀት፣

## 4 የጥራጥሬ ምርቶች ስለማጓጓዝ

### 4.1 የአቅርቦት ጥራጥሬ ምርቶች ስለማጓጓዝ

4.1.1 የጥራጥሬ ምርት የሚጫንበት ከረጢት ከኬሚካል የፀዳ እንዲሁም ለዚሁ አገልግሎት ብቻ የተዘጋጀና ለሌሎች አገልግሎቶች ጥቅም ላይ ያልዋለ መሆን አለበት።

4.1.2 የጥራጥሬ ምርት የሚጓጓዝበት ማጓጓዣ የምርቱን ጥራት በቀላሉ ሊያበላሹ ከሚችሉ ማናቸዉም እንደ ነዳጅ፣ ኬሚካል፣ ቆዳና ሌጦ እና ከመሳሰሉት የፀዳና ከምርቱ ጋር የሚፃረር ባዕድ ነገር በደባልነት ያልጫነ መሆን አለበት፣

4.1.3 የጥራጥሬ ምርት የሚጓጓዝበት ማጓጓዣ እርጥበት፣ ፀሃይ እና አቧራ በማያስገባ ሁኔታ ተሸፍኖ መጓጓዝ አለበት ፣

4.1.4 በአቅራቢዎች ወደ ኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት መጋዘን የሚጓጓዘዉ ምርት አግባብነት ባለዉ የክልል አካል በተመደበ ተቆጣጣሪ የተረጋገጠ ሸኚ ሰነድ መረጃ በመያዝ ማጓጓዝ አለበት፣

4.1.5 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4.1.4 መሰረት አግባብ ባለዉ አካል በተመደበዉ ተቆጣጣሪ የሚሰጠዉ ሸኚ ሰነድ የሚከተሉትን መረጃዎች ማሟለት አለበት

ሀ/ የተሸከርካሪው ሠሌዳ ቁጥር

ለ/ የአሽከርካሪው ሙሉ ስም

ሐ/ የሚያጓጓዘዉ የጥራጥሬ ምርት አይነትና መጠን

መ/ ምርቱ የተሸኘበት ቀን

ሠ/ የምርቱ መነሻ እና መድረሻ ቦታ

ረ/ የምርቱ ባለቤት ሙሉ ስም

### 4.2 ለዉጭ ገበያ የሚቀርብ ጥራጥሬ ምርት ስለማጓጓዝ

4.2.1 የጥራጥሬ ምርት በኮንቴነር ሲላክ የሚጫንበት የኮንቴነር ወለልና ግድግዳዉ ከባዕድ ነገሮች እና ከኬሚካል ቅሪት የፀዳ ሆኖ የአየር ማስገቢያ ቀዳዳ ያለዉ መሆን ይኖርበታል፤

4.2.2 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4.2.1 የሚላኩ የጥራጥሬ ምርቶች ለቁጥጥር በሚያመች ሁኔታ ምርቱ በተዘጋጀበት ቦታ መታሸግ አለበት፤

4.2.3 የጥራጥሬ ምርት የሚጫንበት ከረጢት ከኬሚካል ንክኪ የፀዳ እንዲሁም ለዚሁ አገልግሎት ብቻ የተዘጋጀና ለሌላ አገልግሎት ያልዋለ መሆን አለበት፣

ንግድ ሚኒስቴር Minisstry of Trade Archives መዝገብ ቤት
ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር Ministry Of Trade & Industry Archives መዝገብ ቤት

7.6 ሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት እርከኑን የሚያስተዳድረዉ አግባብነት ያለዉ የክልል አካል የግብይት ቦታዉ በከተማ ክልል የሚገኝ ከሆነ ካርታ እና ፕላን ወይም በገጠር ቀበሌ የሚገኝ ከሆነ ደግሞ የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖረዉ ያደርጋል፣

7.7 አግባብነት ያለዉ የክልል አካል ሁለተኛ ደረጃ የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት እርከን ብዛት እና ስርጭትን ሲወስን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ዉስጥ ማስገባት አለበት፤

(ሀ) ለአምራቾች፣ ለአቅራቢዎች፣ ለጅምላ ነጋዴዎች፣ ለቸርቻሪዎች፣ ለአቀነባባሪዎች፣ ለኅ/ሥ/ ማህበራት እና ለላኪዎች ግብይት ያለዉ አመቺነት፣

ለ) ተሽከርካሪ ለማስገባት እና ለማስወጣት ያለዉ አመቺነት፣

(ሐ) የገበያ መረጃ ሰሌዳ፣ መጫኛ እና ማራገፊያ መደላድል፣ የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ እና የፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ያለዉ መሆን አለበት፣

( መ) በአካባቢው በሚገኙ ቁሳቁሶች ወይም በግንብ ወይም በሸቦ በአስተማማኝ ሁኔታ የታጠረ መሆን አለበት።

(ሠ) ለጅምላ ነጋዴዎች፣ ለአቅራቢዎች፣ ለኅ/ሥ/ማህበራት፣ ለአቀነባባሪዎች ሼድ ሊያሰራ የሚችል መሆን አለበት፣

(ረ) ለቸርቻሪ ነጋዴዎች መገበያያ ቦታ ሊያሟላ የሚችል መሆን አለበት።

## ክፍል አራት

### የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ስርዓት

8 በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የሚፈጸም የግብይት ስርዓት

8.1 የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ሻጭ በሆኑ አምራች አርሶ አደሮች እና አልሚ ባለሃብቶች እና ገገር በሆኑ ሸማቾች/ አምራች ህብረት ስራ ማህበራት እንዲሁም በዘመኑ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸዉ አቅራቢዎች፣ አቀነባባሪዎች፣ ጅምላ እና ቸርቻሪ ነጋዴዎች መካከል ብቻ ግብይቱ የሚከናወን ይሆናል ፣

8.2 ግብይቱ በአቅራቢዎች፣ በሸማች ህብረት ስራ ማህበራት/ዩኒየኖች፣ በአቀነባባሪዎች እና በጅምላ እና ቸርቻሪ ነጋዴዎች ባለቤትነት በተያዘ በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል ትክክለኛነቱ በተረጋገጠ ሚዛን ብቻ መከናወን አለበት፣

ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives
ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር Ministry Of Trade & Industry Archives መዝገብ ቤት

9.6 በሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን ላይ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት በወካይ ናሙና መሰረት በሽያጭ ዉል ስምምነት ሊፈጸም ይችላል፣

9.7 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 9.6 መሰረት ግብይቱ በሽያጭ ዉል ስምምነት የሚፈፀም ከሆነ፦

(ሀ) ገዢ በሆኑ ላኪዎች እና ሻጭ በሆኑ አቅራቢዎች ወይም አምራቾች ወይም ህብረት ስራ ማበራት/ ዩኒየን መካከል የሚደረገዉ የዋጋ ዉል ስምምነት የሚወሰነዉ በገዢ እና ሻጭ መካከል በሚደረግ ድርድር ሆኖ የወቅቱን የገበያ ዋጋ መሰረት ያደረገ ይሆናል፤ እንዲሁም የንብርቱ እርክክብ የሚፈፀመዉ በዉል ስምምነታቸዉ መሰረት በሻጭ መጋዘንወይም በገዢ መጋዘን ወይም ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ላይ ሊሆን ይችላል፣

(ለ) ገዢ በሆኑ ሸማች ተቋማት ወይም ሸማች ህብረት ስራማህበራት ወይም ዩኒየን እና ሻጭ በሆኑ ጅምላ ነጋዴዎች ወይም አምራቾች መካከል በሚካሄደዉ የግብይት ዋጋ የሚወሰነዉ በገዢ እና ሻጭ መካከል በሚደረግ ስምምነት እና በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሰረት ይሆናል፤ እንዲሁም የንብርቱ ርክክብ የሚፈፀመዉ በዉል ስምምነታቸዉ መሰረት በሻጭ መጋዘንወይም በገዢ መጋዘን ሊሆን ይችላል፣

ሐ) ገዢ በሆኑ አቀነባባሪዎች እና ሻጭ በሆኑ አቅራቢዎች ወይም አምራቾች መካከል በሚደረገዉ የሽያጭ ዉል ስምምነት መሰረት ዋጋ የሚወሰነዉ በገዢ እና ሻጭ መካከል በሚደረግ ድርድር እና በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሰረት ይሆናል፤ እንዲሁም የንብርቱ ርክክብ የሚፈፀመዉ በዉል ስምምነታቸዉ መሰረት በሻጭ መጋዘን ወይም በአቀነባባሪዉ መጋዘን ወይም ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ሊሆን ይችላል፣

(መ) የዉል ስምምነት ሰነዱ የጥራጥሬ ምርት አይነት፣ መጠን፣ ደረጃ፣ ግብይት የተካሄደበት ቀንና ቦታ፣ ምርቱ የሚቀርብበትና ክፍያ የሚፈፀምበት ቀንና ቦታ፣ የሁለቱን ተዋዋዮች አድራሻ እና ህጋዊ ማህተም ማካተት አለበት፤

9.8 አግባብነት ያለዉ የክልል አካል የግብይት እና የጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያዎችን መመደብ አለበት፣

## ክፍል አምስት

## የጥራጥሬምርቶች ግብይት ተዋናዮች እና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች መስፈርት

### 10 የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ተዋናዮች መስፈርት፣

#### 10.1 የአቅራቢዎች መስፈርት

ንግድ ሚኒስቴር Minisstry of Trade Archives መዝገብ ቤት
ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር Ministry Of Trade & Industry Archives መዝገብ ቤት

10.3.2 ከመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከል የገዛውን፣ ለሸማቾች የሸጠዉን እና የቀረውን ምርት በዓይነት እና በመጠን ለይቶ አግባብነት ላለው አካል በመደበው ሽኚ ሠራተኛ በተጠየቀ ጊዜ መረጃውን ሊያሳይ የሚችል፣

10.3.3 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣዉን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን ያለዉ መሆን አለበት፣

## 10.4 . የሸማች ህብረት ስራ ማህበራት/ዩኒየኖች መስፈርት

10.4.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣዉን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን እና መጋዘን ያለዉ፣

10.4.2 በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የተመዘገበ ሆኖ የህጋዊ ሰዉነት የምስክር ወረቀት ያለዉ፣

10.4.3 አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለው ቋሚ አድራሻ እና ቦታ ያለው፤

10.4.4 ሰራተኛ በቋሚነት ያሰማራ መሆን አለባቸዉ።

## 10.5 የሸማች ተቋማት መስፈርት

ሸማች ድርጅቶች ወይም ተቋማት የጥራጥሬ ምርቶችን ለሆቴሎች፣ ለዩኒቨርስቲዎች፣ ለማረሚያ ቤቶችና ለፖሊስ ተቋማት፣ ለመከላከያ ሰራዊት ተቋማት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለቸዉ።

10.5.1 የተቋሙን ወይም የድርጅቱን ማንነት የሚገልዕ ማረጋገጫ ማስረጃ ያለዉ መሆን አለበት፣

10.5.2 ከተቋሙ ጋር ህጋዊ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ዉል የተዋዋለና የራሱ የንግድ ፍቃድ ያለዉ ሆኖ ምርቱን ለተቋሙ የሚያቀርብ መሆኑን የሚመሰክር የውል ሰነድ በመረጃነት ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት።

## 10.6 የላኪዎች መስፈርት

10.6.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ፣ የጥራጥሬ ምርቶችን ለውጪ ገበያ አዘጋጅቶ ለመላክ የሚያገለግል በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው የማከማቻ መጋዘን፣ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ እና ማሽኒያ ከረጢት ያለው መሆን አለበት፣

10.6.2 በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል መሰረት ከሶስተኛ ወገን ያገኘው የምድር እና መለስተኛ ሚዛን እንዲሁም የእርጥበት መለኪያ መሳሪያ ያለው መሆን አለበት፤

ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives መዝገብ ቤት
ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives
ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር Ministry Of Trade & Industry Archives መዝገብ ቤት

12 **የአቀነባባሪዎች መስፈርት**

12.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው አግሮ ኢንዱስትሪ ያለዉ መሆን አለበት፣

12.2 በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን እና የእርጥበት መለኪያ መሳሪያ እንዲሁም የኢንቨስትመን ፈቃድ ያለዉ እና ወደ ማምረት ሥራ የተሸጋገረ መሆን አለበት፣

12.3 የጥራጥሬ ምርቶች በማዘጋጀት ሂደት በአካባቢው ማህበረሰብ እና በእንስሳት ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል አኳሃን ቆሻሻን ለማስወገድ የሚያስችል አሰራር የዘረጋ መሆኑ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ መሆን አለበት፣

12.4 አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ ቋሚ አድራሻ እና አገልግሎት መስጫ ያለው መሆን አለበት፣

12.5 ከጥራጥሬ ምርቶች ግብይት እና ጥራት ጋር በተያያዘ እውቀት ያለው ባለሙያ በቋሚነት ያሰማራ መሆን አለበት፡

**ክፍል ስድስት**

**የጥራጥሬ ምርት አምራቾች፣ የግብይት ተዋናዮች እና የአገልግሎት ሰጪ ግዴታዎች**

13 **አጠቃላይ ድንጋጌ**

13.1 የግብይት ተዋናዮች የቦሎቄ፣የባቄላ እና የማሾ ጥራጥሬ ምርቶችን ከታህሳስ አንድ እስከ መጪዉ አመት ህዳር 30 ድረስ ሲሆን የሽምብራ፣ የአኩሪ አተር፣ የጓያ፣ የግብጦ እና የፒገን ቢን ምርቶች ከሆነ ከጥር አንድ እስከ መጪዉ አመት ታህሳስ 30 ድረስ በህግ በተወሰነ የገበያ መድረክ አቅርበዉ የመሸጥ፡፡

13.2 ማንኛዉም ግብይት ተዋናዮች ለግብይት ዘጋጃቸው የጥራጥሬ ምርቶች ውስጥ ጥራት ምርመራ አገልግሎት ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና በነፃ የማቅረብ፤

13.3 የጥራጥሬ ምርቶችን ከአምራች አካባቢዎች ወደ ኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች እና የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት፣ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ሸማቾች ወይም ተቋማት በሚገኙበት አካባቢ ሲያጓጉዝ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አስፈፃሚ አካል ኘሎምኘ ማሳሸግ እና ሕጋዊ መሸኛ ሰነድ የመያዝ፣

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade
Archives
መዝገብ ቤት
ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

እንዲሁም ደረጃዉን የጠበቀ ከረጢት እና የእርጥበት መለኪያ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

15.1.3 ያዘጋጀዉን ጥራጥሬ ምርቶች አቅርቦት መቅረብ በሚገባዉ የጊዜ ገደብ ብቻ ለኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት የማቅረብ እና ምርትን አላግባብ በመጋዘን ያለማከማቸት፣

15.1.4 ከመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከላት የሚያጓጉዟቸውን የጥራጥሬ ምርቶች አግባብ ባለው የክልል አካል በተመደቡ የቁጥጥር ባለሙያዎች ለምርመራ ሲጠየቁ ማስመርመር ይኖርበታል፣

15.1.5 ከመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከላት የገዛዉን የጥራጥሬ ምርቶች ለኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት ማቅረብ እና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የመሸጥ የግብይት እርከን መሸጥ አለበት፣

15.1.6 የጥራጥሬ ምርቶችን ለሌላ አገልግሎት በዋለ እና ንጹህ ባልሆነ ከረጢት ያለማጓጓዝና ያለማከማቸ፣

15.1.7 አንድ አቅራቢ በአካባቢዉ ፍትህ ፅ/ቤት የተረጋገጠ ዉክልና በተሰጠዉ ተወካይ አማካኝነት በአካባቢዉ ከሚገኙት የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ሁሉ ምርት መግዛት ይችላል፤ ሆኖም በአንድ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከል ከአንድ በላይ ተወካይ መመደብ ወይም ማሰማራት የለበትም፤

15.1.8 የአንድን አካባቢ የጥራጥሬ ምርቶች ከሌላ አካባቢ የጥራጥሬ ምርቶች እንዲሁም የአንድን ምርት ዘመን የጥራጥሬ ምርቶች ከሌላ ምርት ዘመን የጥራጥሬ ምርቶች ጋር ሳያደባልቅ መከዘን እና መሸጥ አለበት ፣

15.1.9 ለጥራጥሬ ምርቶች ማከማቻነት በተዘጋጀና ከምርቱ ጋር ተፃራሪ ካሆኑ ከነዳጅ፣ ቆዳና ሌጦ እና ካለተፈቀዱ ኬሚካሎች ንኪኪ ነፃ በሆነ መጋዘን ውስጥ ብቻ ማከማቸት አለበት፤

15.1.10 ምርቱን በሚያጓጉዝበት ወቅት ያልተፈቀዱ ኬሚካሎችን አለመጠቀም፤

15.1.11 ከመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከላት የገዛውን ወደ ኢትዩጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት ያቀረበውን እና በመጋዘን በክምችት የሚገኘዉን የጥራጥሬ ምርት ዓይነት እና መረጃ ለይቶ በመያዝ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ አግባብነት ባለው የክልል አካል ሲጠየቅ ማሳወቅ አለበት፤

15.1.12 በክልሉ ጉዳዩ የሚመለከተዉን አካል ሳያስፈቅድ በአንድ አካባቢ ዉስጥ በሚገኝ ሌላ ቦታ ላይ ተጨማሪ የጥራጥሬ ምርት ንግድ ስራ የሚካሄድበት ድርጅት ማቋቋም የለበትም፣

15.1.13 የንግድ ፍቃዱን በማንኛዉም መልኩ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የለበትም፣

15.1.14 ማንኛውም አቅራቢ ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የገዛውን የጥራጥሬ ምርት ወደ ኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት እና ሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን ሲያጓጉዝ አግባብነት ባለዉ የክልል አካል በተመደበ ተቆጣጣሪ የተረጋገጠ ሸኚ ሰነድ በመያዝ ማጓጓዝ አለበት፣

ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives መዝገብ ቤት
ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives መዝገብ ቤት
ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር Ministry Of Trade & Industry Archives መዝገብ ቤት

15.3.11 የሀገሪቱ የጥራጥሬ ምርቶች ጥራትና ግብይት ከሚጎድፉ ማናቸዉም ድርጊቶች መቆጠብ አለበት ፤

15.3.12 ጅምላ ነጋዴዎች ሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን ለመሸጥ በገቡት ዉል መሰረት ምርቱ ማስረከብ አለበት፤

15.3.13 ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግብይት ስርዓት የገቡ የጥራጥሬ ምርቶችን ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት መግዛት የለበትም፤

15.3.14 የጥራጥሬ ምርቶችን ግብይት ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያ የማክበር ግዴታዎች አለበት፤

## 15.4 የሽማች ህብረት ስራ ማህበራት/ዩኒየኖች ግዴታ

15.4.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣዉን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን እና መጋዘን ማሟላት አለበት ፤

15.4.2 የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበሩ አካባቢ ለሚገኙ ሸማቾች ብቻ ማቅረብ አለበት ፤

15.4.3 ቋሚ አድራሻ እና መሸጫ ቦታ ማሟላት አለበት፤

15.4.4 ባለሙያ በቋሚነት ማሰማራት አለበት፤

15.4.5 የጥራጥሬ ምርቶችን ከመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከላት ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ እርከን የጥራጥሬ ምርቶች የግብይት ማዕከላት ብቻ መግዛት አለባት፤

15.4.6 ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ወይም ከምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ እርከን የገዛውን የጥራጥሬ ምርት ከተመረተበት አካባቢ ውጪ በሚገኝና እንዲሰራበት በተፈቀደለት አካባቢ ለሚገኙ ሸማቾች ማቅረብና መሸጥ አለበት፤

15.4.7 የጥራጥሬ ምርቶች መያዣ ከረጢቶችን ባዕድ ከሆኑ ነገሮች እንደ ነዳጅ፤ቅባት፤ ኬሚካሎች፤ቆዳና ሌጦ የመሳሰሉት ጥራትን ከሚያጓድሉ ነገሮች ጋር ማከማቸት ወይም ማጓጓዝ የለበትም ::

15.4.8 የጥራጥሬ ምርቶችን ግብይት ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያ የማክበር ግዴታ አለባቸዉ ::

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

ንግድ ሚኒስቴር
Minisstry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

15.6.4 የጥራጥሬ ምርቶች መያዣ ከረጢቶች ባዕድ ከሆኑ ነገሮች እንደ ነዳጅ፣ቅባት፣ ኬሚካሎች፣ቆዳና ሌጦ ከመሳሰሉት ጥራትን ከሚያጓድሉ ነገሮች ጋር ማከማቸትና ማጓጓዝ የለበትም

15.6.5 የጥራጥሬ ምርቶችን ግብይት ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያ ማክበር አለበት፣

15.6.6 የንግድ ፍቃድን በማንኛዉም መልኩ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የለበትም ::

## 15.7 የአቀነባባሪዎች ግዴታ

15.7.1 አግባብነት ያለዉ አካል ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው አግሮ ኢንዱስትሪ ያለዉ መሆን አለበት፣

15.7.2 በህግ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን እና የእርጥበት መለኪያ መሳሪያ እና የኢንቨስትመን ፈቃድ ያለዉ ሆኖ ወደ ማምረት ተግባር የተሸጋገረ መሆን አለበት፣

15.7.3 የጥራጥሬ ምርቶችን ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን መግዛት አለበት ፤

15.7.4 ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን የገዛዉን የጥራጥሬ ምርቶች በኢንዱስትሪ በማቀነባበር ለገበያ ማቅረብ አለበት ፤

15.7.5 ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት እና ከምርት ገበያ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን የገዛውን፣ በማቀነባበር ለገበያ ያቀረበውን እና በመጋዘን በክምችት የሚገኘዉን የጥራጥሬ ምርት ዓይነት እና መጠን ለይቶ በመያዝ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ አግባብነት ባለው አካል ሲጠየቅ ማሳወቅ አለበት፤

15.7.6 የጥራጥሬ ምርቶችን በማቀነባበር ሂደት የሚፈጠሩ ለአገልግሎት የማይዉሉ ተረፈ ምርቶችን በአካባቢው ማህበረሰብ እና እንስሳት ጤና ላይ ጉዳት በማያስከትል ሁኔታ ማስወገድ አለበት ፣

15.7.7 የጥራጥሬ ምርቶችን ግብይት ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያ ማክበር አለበት፣

15.7.8 የንግድ ፍቃድን በማንኛዉም መልኩ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የለበትም ::

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

16.1.7 ከላኪዎች የተረከበውን የጥራጥሬ ምርት እስከሚዘጋጅ እና ያዘጋጀውን ምርት ለባለቤቱ እስከ ሚያስረክብ ድረስ የሚያከማችበትን መጋዘን እና የሚገለገልባቸውን ከረጢቶ የምርት ጥራትን ከሚያጓድሉ ባዕድ ነገሮች ንክኪ ነፃ ማድረግ አለበት፣

16.1.8 ከላኪዎች የተረከበውን፣ ያዘጋጀውን እና ለባለቤቱ ያስረከበውን የጥራጥሬ ምርት ዓይነት እና መጠን ለይቶ በመያዝ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ አግባብነት ባለው አካል ሲጠየቅ ማሳወቅ አለበት ፡፡

## 16.2 የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ግዴታ

16.2.1 በባለቤትነት የያዘው ወይንም በኪራይ ውል ከሶስተኛ ወገን የተገኘ ደረጃውን የጠበቀ በቂ ማከማቻ መጋዘን ያለው መሆን አለበት፤

16.2.2 ምርቱን ባከማቸበት መጋዘን ያልተፈቀደ ኬሚካሎችን መጠቀም የለበትም ፣

16.2.3 የአንድን አካባቢ የጥራጥሬ ምርቶች ከሌላ አካባቢ የጥራጥሬ ምርቶች እንዲሁም የአንድን ምርት ዘመን የጥራጥሬ ምርቶች ከሌላ ምርት ዘመን የጥራጥሬ ምርቶች ጋር ሳያደባልቅ መከዘን አለበት፤

16.2.4 ተረክቦ ያከማቸውን የጥራጥሬ ምርት ዓይነት፣ መጠን እና የጥራት ደረጃ ጠብቆ በገባው የውል ስምምነት መሠረት በወቅቱ ለባለቤቱ ማስረከብ አለበት፣

16.2.5 ለማከማቸት የተረከበውን፣ ለባለቤቱ መልሶ ያስረከበውን እና በመጋዘን በክምችት የሚገኘዉን የጥራጥሬ ምርት ዓይነት እና መጠን ለይቶ በመያዝ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ አግባብነት ባለው አካል ሲጠየቅ ማሳወቅ አለበት ::

## 16.3 የአጓጓዦች ግዴታ

16.3.1 የሚያጓጓዘዉን የጥራጥሬ ምርቶች አይነትና መጠን አጓጓዡ አረጋግጦ መረከብ አለበት ፣

16.3.2 ማንኛዉም የጥራጥሬ ምርትን አጓጓዥ ከአቧራ እና ከፀሀይ እንዲሁም ከዝናብ በማያስገባ ሁኔታ ማጓጓዝ አለበት፣

16.3.3 የጥራጥሬ ምርትን ከመጓጓዙ በፊት በግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪዎች የመሸኛ ሰነድ መረጃ ይዞ ማጓጓዝ አለበት፣

16.3.4 የጥራጥሬ ምርትን ጥራት ከሚያጓድሉ እንደ ኬሚካል፤ ፈሳሽ፣ ነዳጅ፣ እንስሳት፣ ቆዳና ሌጦ የመሳሰሉትን ባዕድ ነገሮችን ቀላቅሎ ማጓጓዝ የለበትም፣

Ministry of Trade Archives
Ministry of Trade Archives
Ministry Of Trade & Industry Archives

ለ/ የጥራት ቁጥጥር ባለሙያ

1. ስለ ጥራጥሬ ምርቶች ግብይት በቂ ዕውቀት ያለውና በመልካም ስነምግባሩ የተመሰከረለት መሆን አለበት፤

2. ቢያንስ ዲፕሎማ ያለውና በተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት መስኮች የሰለጠነ ሆኖ በዕፅዋት ሳይንስ፣ በጠቅላላ እርሻ፣ በአግሮኖሚ፣ በአግሪቢዝነስ እና በአግሮ ኢኮኖሚክስ ሆኖ በሙያዉ ተጨማሪ የስራ ልምድ ያለዉ መሆን አለበት ።

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በጥራጥሬ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ላይ ተጨማሪ ሥልጠናዎችን ያገኘ ቢሆን ይመረጣል።

4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወይም አግባብነት ያለው የክልል፤የዞን እና የወረዳ አካል በሚመድበው ቦታ ለመስራት ፈቃደኛ መሆን አለበት፣

18 የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት

18.1 የፌዴራል የጥራጥሬ ምርቶች ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ/ አዲስ ፈቃድ አውጥተው በጥራጥሬ ምርት ላኪነት የሚሰማሩ ድርጅቶችን ብቃት በየጊዜው በመገምገም የግብይትና የምርት ጥራት አጠባበቅ አቅማቸው እንዲጎለብት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

ለ/ ላኪ ድርጅቶች በጥራጥሬ ምርት ግብይት ደንብ እና መመሪያ ላይ በተፈቀዱ አሰራሮች መሠረት እና ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ እና ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን ብቻ ምርት እንዲገዙ ያስገነዝባል፤ አፈፃጸሙንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ሐ/ ላኪ ድርጅቶች ከኢትዩጵያ ምርት ገበያ እና ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን የገዟቸውን የጥራጥሬ ምርቶች በተፈቀደላቸው የማዘጋጃ ኢንዱስትሪ እና የማከማቻ መጋዘን ብቻ ማዘጋጀታቸውንና ማከማቸታቸውን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፣

መ/ ላኪ ድርጅቶች ወደ ውጪ በሚልኩት የጥራጥሬ ምርት ከረጢት ላይ የምርቱን ዓይነት፣ መጠን፤ የጥራት ደረጃ፤ የላኪ ድርጅቱን ስም፣ በኢትዮጵያ የተመረተ መሆኑን እንዲሁም የሚሄድበትን አገር እና የገዢ ኩባንያውን ስም የሚገልጽ ጽሁፍ የታተመበት መሆኑን ያረጋግጣል፣

ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives መዝገብ ቤት
ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር Ministry Of Trade & Industry Archives መዝገብ ቤት

ሠ/ በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት እና በሁለኛ ደረጃ የግብይት እርከን የተስተካከለ የግብይት ስርዓት መሰፈኑን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

ረ/ የጥራጥሬ ምርት ሲጓጓዝ አስፈላጊ መረጃ ያለስርዝ ድልዝ እና እዉነተኛ መረጃ በመሙላት ዲስፓቹ ላይ በየደረጃዉ ባሉ የክልሉ ንግድ ሴክተር መ/ቤት ህጋዊ መህተም በማድረግ መሸኘት፣

ሰ/ የግብይት ተዋናዎች በጥራጥሬ ምርት ግብይት ደንብ እና መመሪያ ላይ በተፈቀዱ አሰራሮች መሠረት ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት እና ከሁለተኛ ደረጃ የግብይት እርከን ምርት እንዲገዙ ያስገነዝባል፤ አፈፃጸሙንም ይከታተላል፣

ሸ/ በጥራጥሬ ምርት ግብይት ላይ የተሰማሩ አካላትን ወይም ድርጅቶችን ብቃት በየጊዜው በመገምገም የግብይትና የምርት ጥራት አጠባበቅ አቅማቸው እንዲጎለብት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

ቀ/ የጥራጥሬ ምርቶች መያዣ ከረጢቶችን ባዕድ ከሆኑ ነገሮች እንደ ነዳጅ፣ ቅባት፣ ኬሚካሎች፣
ቆዳ እና ጥራትን ከሚያጓድሉ ነገሮች ጋር ማከማቸት ወይም መጓጓዝ እንደሌለበት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

በ/ የጥራጥሬ ምርቶች ግዥና ሽያጭ አይነት እና መጠን፣የዋጋ ዝርዝር እንዲሁም ለግብይት ስርዓት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች በመያዝ ፣በማደራጀት እና በመተንተን ጥቅም ላይ እንዲዉል ያደርጋል፣

ተ/ ጥራጥሬ ምርቶች መቅረብ በሚገባዉ የጊዜ ገደብ ብቻ ለኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት ድርጅት የማቅረብ እና ምርትን አላግባብ በመጋዘን እንዳይከማች የማስገንዘብ፣ የመከታተል ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡

Ministry of Trade Archives
Ministry of Trade Archives
ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር Ministry Of Trade & Industry Archives መዝገብ ቤት